# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፪፣ ሚያዚያ ፳፻፲፫ ዓ.ም


**ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ** በሚል ርዕስ በየሁለት ወሩ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እየተዘጋጀች የምትሰራጨው ይህቺ ዜና መፅሄት የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ለመቀነስ የተዘጋጀውን ዕቅድና አፈፃፀሙን በተመለከተ መረጃዎችንና አዳዲስ እውቀቶችን ለተለያዩ ባለድርሻዎች የማድረስ ዓላማ አላት፡፡




“ኢትዮጵያውያን እና የአፍሪካ ቀንድ ህዝቦች በአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ ተጠቂዎች ናቸው፡፡”

ክቡር ፕ/ር ፍቃዱ በየነ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ኮሚሽነር

## በዚህ እትም. . .


| | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ የሙቀት አማቂ ጋዞች የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ (MRV) ስርዓትና የአፈፃፀም ደረጃ - ክፍል 1 | ፪ |
| ዜናዎች | ፪ |
| ሁነቶች | ፫ |
| የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት ትግበራ አፈፃፀም በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ | ፯ |
| ልዩ ልዩ ህትመቶች | ፯ |





**ዋና አዘጋጅ፡** ንጉሱ ለማ ገብሬ

**አዘጋጆች፡** ተስፋዬ ጋሻው፣ ሙሉነህ ገ/ሄደቶ፣ በእምነት ተሾመ እና ሮቢ ረዳ

**አምደኞች፡** መንሱር ደሴ እና መሀመድ አንዶሼ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡** አርሴማ አንዳርጋቸው

## ዜናዎች

### የሶማሌ ክልል አካባቢ ጥበቃ ቢሮ የአፍሪካ ቀንድ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤን አስተናገደ

“የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖዎችን ማጣጣምና አይበገሬነትን መገንባት በአፍሪካ ቀንድ እይታ” በሚል መሪ ሀሳብ የተመራ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ በሶማሌ ክልል መንግስት የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ቢሮ አስተናጋጅነት ከኤፕሪል 22 - 23 በጅግጅጋ ከተማ ተካሂዷል። ጉባኤው በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ በሚገኙ ሀገራት ላይ የተከሰቱ አበይት የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖዎችን በመለየት ተስማሚ መፍትሄዎችን እና የወደፊት እርምጃዎች በጋራ ለመንደፍ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

በጉባኤው ላይ ከአፍሪካ ቀንድ አባል ሀገራትና ከፌደራል የዘርፍ መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ ታዳሚዎች ተካፍለዋል። ጉባኤውን በንግግር የከፈቱት የኢፌዲሪ አካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ፕሮፌሰር. ፍቃዱ በየነ እንዳሉት ኢትዮጵያውያን እና የአፍሪካ ቀንድ ህዝቦች የአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ ጫና አድርሶባቸዋል። ይህም የተራዘመ ድርቅ፣ የጎርፍ መጥለቅለቅ እና የአንበጣ ወረራን የሚያስከትል ሲሆን በማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ፤ የኃይል አቅርቦት፣ የግብርና ምርታማነት እና የምግብ ዋስትና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያደርሳል። ምንጬ

### የመጀመሪያው የሥርዓተ-ፆታ እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚቴ አውደ ጥናት ተካሄደ

የሥርዓተ-ፆታ እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚቴ እ.ኤ.አ. ታህሳስ 2020 ተቋቋመ። የተቋቋመበት ዋና ዓላማ በዘርፉ የሚገኙ ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ያላቸውን ዕውቀት እና ልምዶችን በማስተባበር የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጭ እና ሁሉን አቀፍ የአየር ንብረት እርምጃን የሚያረጋግጡ አቅሞችን ለማጠናከር ነው። የመጀመሪያው ስብሰባ እ.ኤ.አ. ኤፕሪል 26፣ 2021 የተካሄደ ሲሆን በወቅቱም ኮሚቴው የሚሰራበትን የመግባቢያ ሰነድ ለመቅረፅና ለአንድ ዓመት ያህል የሚተገበር የጋራ መርሀ ግብር ለማውጣት እንዲሁም በሲ.ዲ.ኬ.ኤን የተዘጋጁ የስርዐተ-ፆታና አካታች የአየር ንብረት ለውጥ ፕሮግራሞች ላይ ያተኮሩ የማሰልጠኛ ሰነዶች ለማስተዋወቅ እና ለማጋራት ነው።

የውይይት መድረኩን በንግግር የከፈቱት በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የአየር ንብረት ለውጥና ብዝሃ ሕይወት ዘርፍ ዋና ዳይሬክተር አቶ ንጉስ ለማ እንዳሉት የአየር ንብረት ለውጥ ላይ ያተኮሩ እንቅስቃሴዎች፣ የፆታ እኩልነትን እና ሁሉን አቀፍነትን እንዲያካትቱ በተለያዩ ባለድርሻዎች መካከል ያለው ቅንጅት በጣም አስፈላጊና ቀጣይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው።

አውደ ጥናቱ በገንዘብ ሚኒስቴርና በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ድይሬክቶሬት የተዘጋጀ ሲሆን በሲ.ዲ.ኬ.ኤን እና ጂ.ጂ.አይ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጎለታል።

### የኢትዮጵያ የሙቀት አማቂ ጋዞች የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ (MRV) ስርዓትና የአፈፃፀም ደረጃ - ክፍል 1

- ❑ በንቲ ፈርዲሳ ዱጋሳ፣ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ብሄራዊ የሙቀት አማቂ ጋዞች ስረዐት ዝርጋታ ዳይሬክተር

የፓሪስ ስምምነት የአየር ንብረት ለውጥ ማስተሰረያ ተግባራትን ለመለካት አለም አቀፍና ምቹ የሆነ የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓት ፈጥሯል። የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓት፤ ለፓሪስ ስምምነት የቀረበውን የሀገሪቱ የአየር ንብረት ለውጥ የማስተሰረያና የማጣጣሚያ ግቦችና ፖሊሲዎች የያዘውን በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ (NDC) ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር ያስችላል። የልኬት ስራ የልቀትን አጠቃላይ ሁኔታ፣ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ለመቀነስና የትኞቹ ተግባራት ላይ ማተኮር እንደሚያስፈልግ ለመለየት፣ የማስተሰረያ ስራዎች ላይ የተገኙ ድጋፎችን ለመከታተል፣ በNDC ውስጥ የታቀዱትን የማስተሰረያ ተግባራት ውጤታማ መሆናቸውን ለመገምገም፣ የተገኙ ድጋፎችን ውጤታማነትን ለመመዘንና የሙቀት አማቂ ጋዞች ቅነሳ ሂደትን ለመከታታል ያስፈልጋል። የመዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓቶች ደግሞ ግልፀኝነትን፣ መልካም አስተዳደርንና ተጠያቂነትን ለማስፈን፣ የተገኘውን ውጤት ተዓማኒነት ለማረጋገጥና ግብዓቶች ውጤታማ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ይረዳሉ። ሶስት አይነት የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓቶች አሉ፤

**የሙቀት አማቂ ጋዞች የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓት** ማለት በተወሰነ ጊዜ የልቀት መጠንን መገመት፣ ሪፖርት ማድረግና ማረጋገጥ ነው። ይህ አይነቱ የሙቀት አማቂ ጋዞች የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓት፤ በሀገር ደረጃ፣ ወይም በታችኛው አስተዳደር እርከን በሚገኙ ድርጅቶችና ተቋሞች ሊተገበር ይችላል።

**የማስተሰረያ ተግባራት፤ የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓት** የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ቅነሳ እና/ወይም የፖሊሲ፣ ፕሮጀክቶችና የተለያዩ ተግባራት ያላቸውን የዘላቂ ልማት ውጤት መገምገም ከዚህ በተጨማሪ ያላቸውን የትግበራ ሂደት መቆጣጠርን ያካትታል።

**ወደ ገፅ ፫**

**ከገፅ ፪ የቀጠለ..**

እንደ ምሳሌነት የመንግስት የቤት ሙቀት መከላከያ የድጎማ ፕሮግራም የሙቀት አማቂ ጋዝ ቅነሳ እና የስራ ዕድል ፈጠራ ላይ ያለውን ተፅዕኖዎች መጥቀስ ይቻላል፡፡

የሙቀት አማቂ ጋዞች የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓት በቀጥታ የልቀት መጠንን ሲለካ፤ የማስተሰረያ ተግባራት የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓት የልቀትን ለውጥና ሌሎች ከሙቀት አማቂ ጋዝ ጋር በቀጥታ የማይያዙ ነገርግን ከነዚህ ተግባራት የሚገኙ ለውጦችን ጭምር ይለካል፡፡

**ድጋፎችን የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓት** የተገኙ የገንዘብ ፍሰቶች፣ ቴክኒካልና የአቅም ግንባታ ድጋፎችን መከታተል እና የድጋፎችን ውጤትና ተፅዕኖዎች መገምገም ላይ ያተኩራል፡፡ ታዳጊ ሀገራት ከአየር ንብረት ጋር የሚያያዙ ከሁለትዮሽና ሌሎች በርካታ ቻናሎች የሚገኙ የፋይናንስ ድጋፎችን መከታተል ለዚህ እንደ ምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

## የኢትዮጵያ አለም አቀፍ ቁርጠኝነት

በአለም አቀፍ ስምምነት መሰረት ኢትዮጵያ ከ1982-1987 ዓ.ም ያለውን የመጀመሪያ ብሔራዊ ኮምዩኒኬሽን ለUNFCCC አስገብታለች፡፡ ከዚህም በመቀጠል መንግስት 60 የማስተሰረያ ተግባራትን፤ ዘርፎችን መሰረት ባደረገ መንገድ የለየ ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ስትራቴጂ ነድፏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ መንግስት የተለያዩ ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና የድርጊት መርሐ-ግብሮችን የነደፈ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ፣ ሀገራዊ የማጣጣሚያ የድርጊት ፕሮግራም (NAPA)፣ የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ፕሮግራም (EPACC)፣ REDD+፣ የኢነርጂ፣ የውሀ፣ የግብርናና የገጠር ልማት የአልበገሬነት ስትራቴጂዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህም የአየር ንብረት ለውጥ የማጣጣሚያና የማስተሰረያ ስራዎችን ለመተግበር የሚረዳ ሀብት ለማፈላለግ ህጋዊ መሰረት ሲፈጥር፤ ከዚህም በተጨማሪ የአየር ንብረት ለውጥን ሀገራዊ ዕቅድ ውስጥ ማጉላትን ማድረግ ያካትታል፡፡

ሁለተኛው ሀገራዊ ኮምዩኒኬሽን ከ1986-2005 ዓ.ም ላለው ጊዜ ተዘጋጅቶ በ2007 ዓ.ም ገብቷል፡፡ ይህ ሀገራዊ ኮምዩኒኬሽን የመጀመሪያው ሀገራዊ ኮምዩኒኬሽን ቀጣይ ሲሆን የአለም አቀፍ ኮንቬንሽን ቀጣይ ስራዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

## የሀገር ውስጥ መለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓት

የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን፤ ለአለም አቀፉ የሪፖርት ሂደት ግልፀኝነትን ለማሳደግና በአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ መሰረት ሀገራዊ ኮምዩኒኬሽንና በየሁለት አመቱ የሚዘጋጅ ሪፖርትና ወቅታዊ የሆነ የሙቀት አማቂ ጋዝ ሀገራዊ መረጃ ዝርዝር ለማዘጋጀት ዕቅድ አስቀምጧል፡፡

ለዚህም ባለፉት 3 ዓመታት የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ዘላቂና ጠንካራ የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓት ለመዘርጋት መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ሲሰራ ቆይቷል፡፡

## ሀገራዊ የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ማዕቀፍ

ኢትዮጵያ ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ዕድገት የላቀ ግብ በያዘው ዕቅዷ መሰረት ለአረንጓዴ ዕድገት ዕቅድ ዝግጅትና ግምገማ፤ ጠንካራ፣ ትክክለኛና ተዓማኒ የመረጃ ስርዓት ያስፈልጋታል፡፡ ይህም ተቋማዊ መዋቅርን ማልማት እና በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን መረጃ ለማሰባሰብ፣ ሪፖርት ለማድረግ፣ ለመገምገምና በቅንጅት ለማስቀመጥ የሚያስችል ስርዓት ይፈልጋል፡፡

በ2008 ዓ.ም የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን. በአለም አቀፉ የአረንጓዴ ዕድገት ኢንስቲትዩት (GGGI) ድጋፍ ዘላቂ ስርዓት ለመፍጠር የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ማዕቀፍ አቋቁሟል፡፡ ይህም ማዕቀፍ የሚከተሉት ሁኔታዎችን ለማከናወን ይጠቅማል፤

- ለመረጃ ምንጭነት ግልፅ በሆነ መልኩ ተግባርና ሀላፊነት ለይቶ የሚያስቀምጥ ከወረዳ፣ ክልልና ፌዴራል ተግባሪ አካላት ጋር ተቋማዊ መዋቅርን መዘርጋት፤
- ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የሚገኝ የመረጃ ፍሰትን የሚያሳልጥ የመረጃ አስተዳደር ስርዓት (ሀገራዊ የልኬትና ልየታ ስርዐት) መዘርጋት፤
- በሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ልየታና ልኬት ሂደት ላይ ለተሰማሩ ተጠቃሚዎች በመልካም ተሞክሮ ላይ መመሪያ በመስጠት ሂደቱ አሻሚ እንዳይሆንና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ማስቻል፤
- ባለድርሻ አካላትን በማማከር ሁሉም የተስማማበት የመረጃ ልውውጥ አሰራር ለመዘርጋት ይረዳል፡፡

**ወደ ገፅ ፬**

ከገፅ ፫ የቀጠለ

**መዋቅራዊ ዝግጅትና የመግባቢያ ሰነድ**

የትግበራ መረጃ፣ የልቀት መጠንና የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን የያዘ የማዕቀፉን ተግባራዊነት ቀጣይነት ያለው ሪፖርት ልውውጥ ለማረጋገጥ በ6 ዘርፍ ሚ/መ/ቤቶችና በ2 ኤጀንሲዎች መካከል የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሟል፡፡

መ/ቤቶቹም፤ ግብርና፣ ውሀ፣ መስኖና ኢነርጂ፣ ትራንስፖርት፣ ማዕድንና ፔትሮሊየም፣ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን፣ ንግድና ኢንዱስትሪ፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክና የኢትዮጵያ ካርታ ስራዎች ኤጀንሲ ናቸው፡፡ የመግባቢያ ሰነዱ ለሙቀት አማቂ ጋዝ ልኬት የሚያስፈልግ፤ የእያንዳንዱን ተቋም ተግባርና ሀላፊነት እና የትግበራ መረጃ በአለም አቀፉ የአየር ንብረት ለውጥ ፓነል (IPCC) መመሪያ መሰረት የያዘ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም እያንዳንዱ መ/ቤት ይህንን ስራ የሚከታተል ቋሚ የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ባለሙያ መድቧል፡፡




**ስዕል 1፡ ሀገራዊ የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓት መዋቅራዊ ዝግጅት**

ወደ ገፅ ፭

## ሁነቶች

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለማቀፍ ደረጃ መከሰቱንና በፍጥነት መስፋፋቱን ተከትሎ በርካታ የአየር ንብረት ለውጥና ዘላቂ የአካባቢ ልማትና ጥበቃን የተመለከቱ ሁነቶች በመረጃ ቴክኖሎጂ በመታገዝ እየተካሄዱ ናቸው። የሚከተሉት በበይነ መረብ አማካይነት የሚከናወኑ ሁነቶች ለማናቸውም ታዳሚዎች ተደራሽ ናቸው። እያንዳንዱን ሁነቶች አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ እባክዎ ‹ምንጭ› የሚለውን ማስፈንጠሪያ ይክፈቱት።

- የበየነ መረብ የአቻ መማማሪያ ጉባኤ -በተቀናጀ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሾች የአየር ንብረት ለውጥን ተፅኖ መቋቋም፤ የማጣጣምያና ማስተሰሪያ ስልቶችን ማቀናጀት፤ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣም ዓለማቀፍ ጥምረትና ዝቅተኛ የልቀት ልማት ስልቶች ዓለም አቀፍ አጋርነት ፣ ግንቦት 2021 | ምንጭ
- ዘላቂ የምርትና የፍጆታ ተጋላጮች የትንተና መሣሪያዎች ክልላዊ አውደ ጥናቶች ፣ GO4SDGs ፣ ግንቦት 2021 | ምንጭ
- የመሬት ዋጋና ፍትሃዊ ልማት ፣ ደብልዪ. አር. አይ፣ ግንቦት 2021 | ምንጭ
- የዘላቂ የልማት ግቦች ፋይናንስ የጀኔቫ ጉባኤ 2021፣ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም፣ ሰኔ 2021 | ምንጭ
- 9ነኛው ዓለማቀፍ የስነ-ምዳር ጥበቃ ኮንፈረንስ፣ ማህበረሰብ ለስነ-ምዳር ጥበቃ ማህበር፣ ሰኔ 2021 | ምንጭ
- በአጽኦት ማሰብ ተከታታይ ፕሮግራም፤ ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ መፍትሄዎች፣ ክላይሜት አክሽን፣ ሰኔ 2021| ምንጭ
- በአጽኦት ማሰብ ተከታታይ ፕሮግራም፤ ውቅያኖሶችና ውሀ-ወለድ ኢኮኖሚ፣ ክላይሜት አክሽን፣ ሰኔ 2021 | ምንጭ
- በአጽኦት ማሰብ ተከታታይ ፕሮግራም፤ የመሬት አጠቃቀምና እርሻ፣ ክላይሜት አክሽን፣ ሰኔ 2021 | ምንጭ
- የአየር ንብረት የፈጠራ መድረክ 2021 ፣ ክላይሜት አክሽን፣ ሐምሌ 2021 | ምንጭ


**ከገፅ ፬ የቀጠለ..**


### ዓመታዊ ሀገራዊ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልየታና ልኬት

ወቅቱን የጠበቀና ዘላቂ የሆነ የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን ሪፖርት (ሀገራዊ ኮምዩኒኬሽን) እና በየሁለት ዓመቱ የሚዘጋጅ ሪፖርት ለUNFCCC እና EFCCC ለማስገባት እንዲያስችል፤ ሀላፊነት ላለበት የመንግስት አካል የዘርፍ ሚ/መ/ቤቶች በየዓመቱ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትና ቅነሳ ሪፖርት እንዲያደረጉ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።

ዓመታዊ የሙቀት አማቂ ጋዝ ሪፖርትን ማጠናከር፡ ቀጣይነት ያለውና ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት ከማዘጋጀት በተጨማሪ የትግበራ መረጃ ዘገባ፣ የልቀት ፋክተር እና ሀገራዊ ኮምዩኒኬሽን በየሁለት ዓመቱ የሚዘጋጅ ረፖርት ለማዘጋጀት ይረዳል። በዚሁ መሰረት (በመግባቢያ ሰነዱ ላይ ተመስርቶ) በዘርፎች የሚቀርበው የሙቀት አማቂ ጋዝ ሪፖርት የኢትዮጵያ የ3 ዓመት የሙቀት አማቂ ጋዝ ሪፖርት ተዘጋጅቷል። የዚህ የ3 ዓመታት ሪፖርት አላማ፡ የልቀት ዋነኛ ምንጭ/መከማቻ፣ የዘርፎችን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ለመገመትና ከአለም አቀፉ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትና ማስወገድ ጋር በማነፃፀር ውሳኔ መስጠት ማስቻል ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ የማሰተሰረያ ዘዴዎችን በመተግበር የተገኙ ውጤቶች የሙቀት አማቂ ጋዝ ቅነሳን በማሳካት ረገድ ያለውን ደረጃም ይከታተላል። ከዚህም በተጨማሪ ሪፖርቱ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ለውሳኔ ሰጪዎች፣ ለሀገራዊና አለም አቀፋዊ ባለድርሻ አካላት ለማቅረብ ይረዳል።

ሪፖርቱ የተዘጋጀው ለሰስት ዓመታት (2007-2009 ዓ.ም) እና ለ5 ዓመታት (2006-2010 ዓ.ም) ሲሆን የተካተቱት ዘርፎችም ኢነርጂ፣ የኢንደስትሪ የምርት ሂደትና ምርት አጠቃቀም፣ ግብርና (ከደንና ሌሎች መሬት አጠቃቀም ውጪ) እና ቆሻሻ ሲሆኑ ካርቦንዳይ ኦክሳይድ፣ ሜቴን እና ናይትረስ ኦክሳይድ ጋዞችን ያጠቃልላል።

### የአቅም ግንባታ

የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ ስርዓት መዘርጋት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እንደ WRI፣ EU፣ FAOና CSU/USFS ያሉ አለም አቀፍ ድርጅቶችና የልማት አጋሮች የአቅም ግንባታ ድጋፎች ሲያደርጉ የቆዩ ሲሆን ይህም ዘላቂ ስርዓትን ለመፍጠር የሚያስችል ስልጠና፣ የፋይናንስና ቴክኖሎጂ ድጋፍን ያጠቃልላል። ይህም በተሻለ ሁኔታ ያለውጪ ሀይል ድጋፍ በራስ አቅም ስራዎችን ለመስራትና ሪፖርቶችን ለማዘጋጀት አስችሏል።

በቀጣይ ክፍል የአዲስ አበባን የሙቀት አማቂ ጋዝ ዝርዝር የሚመለከት ጠቅለል ያለ ሪፖርት ይዘን እንቀርባለን።

# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፩፡ ቁጥር ፩


## ልዩ ልዩ ህትመቶች

### የማቀዝቀዣዎች አቅራቢዎች፤ የዜሮ ልቀት ውድድሩን የሚያሸነፈው ማን ይሆን?




ይህ ሰነድ የማቀዝቀዣዎች አምራች ኢንዱስትሪዎችን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖዎች ቅነሳ ግዴታዎች ገፅታ በአጭሩ ለማስረዳት ያለመ ነው። ሰነዱ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ወደ ዜሮ ለማውረድ የተጀመረውን ዘመቻ የዝግጅት ምዕራፍ ክንውኖች ለመቀላቀልና በቅርቡ ከታተመው ማቀዝቀዣዎችን ለአየር ንብረት ለውጥ እርምጃ ወደ ዜሮ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ መዳረሻ አድርጎ በማጣጣም መተግበርን ይመለከታል። ምንጭ

### በአየር ንብረት ለውጥ ኢኮኖሚያዊ እንድምታዎች ላይ ያለው መግባባት




ይህ ሰነድ በአየር ንብረት ኢኮኖሚያዊ እንድምታዎች ላይ ሰፊ ናሙናን ያካተተ ዓለም አቀፍ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የአየር ንብረት ለውጥን አለመከላከል የሚያስከትላቸው ወጪዎች ለመከላከል ከሚደረጉ ወጪዎች እንደሚበልጡ ስምምነት እንዳል እንዲሁም አፋጣኝ የአማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ያሳያል። ምንጭ

### የአየር ንብረት ለውጥ አፈፃፀም ማውጫ 2021




የአየር ንብረት ለውጥ አፈፃፀም መረጃ ጠቋሚ ኢንስቲትዩት (CCPI) በ57 ሀገሮች (የአውሮፓ ህብረትን ጨምሮ) የአየር ንብረት ለውጥ ጥበቃን በከፍተኛ የልቀቶች መጠን ይተነትናል፤ ያነፃፅራል። እነዚህ ሀገሮች አንድ ላይ ሲደመሩ 90 ከመቶ የሚሆነውን የዓለም ልቀትን ይይዛሉ። መረጃ ጠቋሚው በዓለም የአየር ንብረት ፖለቲካ ውስጥ ግልፅነትን ለማሳደግ እና በተናጥል ሀገሮች የተደረጉትን የመከላከል ጥረቶችንና መሻሻሎችን በንፅፅር ለማየት ያስችላል። ምንጭ

## የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት ትግበራ አፈፃፀም በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ

- ገብረ ሚካኤል ገ/ኪዳን፤ የኢንዱስትሪ አካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር (ንኢሚ)

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ተዘጋጅቶ በመተግበር ላይ የሚገኘው የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ (CRGE) እንደሚያመለክተው የልማት ስልቱ በየዘርፉ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያና ማስተሰርያ ስርዐትን ተግባራዊ በማድረግ እ.አ.አ. በ2025 ከካርበን ልቀት ነፃ የሆነና መካከለኛ ገቢ ላይ የደረሠ ኢኮኖሚን የመገንባት ራዕይን ቀይሷል።

በዚሁ ሀገራዊ ማዕቀፍ ውስጥ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት ትግበራ ከዘፉ እንዲቀነስ የሚጠበቀው የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ለመገደብ የሚረዱ የተለያዩ እርምጃዎችን ለይቷል። በለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት መሠረት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው እ.አ.አ. እስከ 2030 ድረስ ከሚለቀቀው የሙቀት አማቂ ጋዞች ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚያበረክተው እንደሚሆን ይታመናል ።

የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት በዘልማዳዊ አካሄድ ከቀጠለ የዘርፉ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት በየዓመቱ በ16% እንደሚያድግ ተተንብዩል። ይህም ማለት ልቀቱ እ.አ.አ. በ2010 ከነበረበት 4 ሜትሪክ ቶን የካርበን ዳይኦክሳይድ እኩሌታ እ.አ.አ. በ2030 ወደ 71ሜትሪክ ቶን የካርበን ዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ ያድጋል ማለት ነው።

በከባቢ አየር ውስጥ የሙቀት አማቂ ጋዞች ክምችት መበራከት ለአየር ንብረት ለውጥ አስጊ የሆነው የዓለም ሙቀት መጨመርን አስከትሏል፤ ይህም እውነታ የአየር ንብረት ለውጥን አባብሶታል። የሙቀት አማቂ ጋዞች የሚከሰቱት ከተለያዩ የኢንዱስትሪ ተግባራት ነው። የሙቀት አማቂ ጋዞች ዋና የልቀት ምንጮች ቁሳቁሶችን በምርት ሂደት በኬሚካላዊ ወይም በቁሳዊ ሁኔታ የሚቀይሩ የኢንዱስትሪ ሂደቶች ናቸው ። በእነዚህ ሂደቶች ወቅት ካርቦን ዳይኦክሳይድን ($Co_2$) ጨምሮ በርካታ የሙቀት አማቂ ጋዞች ማለትም ሜቴን ($CH_4$)፣ ናይትረስ ኦክሳይድ ($N_2O$)፣ ሃይድሮ ፍሎሮካርቦኖች (HFCs) እና ፐር-ፍሎሮካርቦኖች (PFCs) ሊመረቱ ይችላሉ።

የተባበሩት መንግስታት የ 2015 የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ

**ወደ ገፅ ፯**

**ከገፅ ፮ የቀጠለ...**

ስምምነት አካል እንደመሆኗ መጠን ኢትዮጵያ በማዕቀፉ ውስጥ የሚተገበር በብሔራዊ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ እቅድ መሠረት ሀገሪቱ ከኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ወደ 20 ሚሊዮን ቶን የካርበን ዳይኦክሳይድ እኩሌታ (CO2e) ለመቀነስ ቃል ገብታለች። ይህም ተግባራዊ የሚደረገው የኢንዱስትሪው ዘርፍ ባስቀመጠውና "ወደ ዘመናዊ እና ኃይል ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች በፍጥነት መሸጋገር" በሚል መሪ ሀሳብ አማካይነት ነው። የሚከተሉት ስትራቴጂዎች የኢንዱስትሪ ዘርፍን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን የሚገድቡ እና በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ተፅኖዎች ለመቀነስ የተጣሉ ግቦችን ለማሳካት የሚያስችሉ ስልቶች ተለይተዋል።

- የኃይል ቆጣቢነት (ለምሳሌ ፣ ፋብሪካዎች ዘመናዊ የምርት ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ማዘጋጀት፣ የሙቀት ብክነትን ማሻሻል፣ ቆሻሻዎችን ለሀይል ምንጭነት መልሶ እና አድሶ መጠቀም)
- አማራጭ ነዳጆች (ለምሳሌ ከድንጋይ ከሰል / ከእቶን ዘይት ወደ ባዮማስ / ባዮ ነዳጅ ወይም ኤሌክትሪክ መቀየር)
- አማራጭ የምርት ሂደቶች (ለምሳሌ ኬሚካሎችን በኢንዛይሞች መተካት፣ ክሊንከር መተካት)
- ከኢንዱስትሪ ሂደቶች የሚወጣውን ካርቦን መያዝ እና የካርቦን ምርትን እንደ ግብዓት ለሚጠቀሙ ሌሎች ኢንዱስትሪዎች ማቅረብ።

## የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት የትግበራ ፍኖተ-ካርታ

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት የትግበራ ፍኖተ ካርታ የተቀረፀው በንግድና ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተቀመጡ ተግባራትን በመደገፍ በሀገር ደረጃ የተቀመጡ ዓላማዎችንና የተጣሉ ግቦችን በመደገፍ ተግባራቱ ውጤታማ እንዲሆኑ በሚያስችል ሁኔታ ነው። በዚሁ መሠረት ፍኖተ ካርታው እያንዳንዱን እርምጃዎች በቴክኖሎጂዎች ፣ በአቅም እና በገንዘብ ረገድ ምን ድጋፍ ሊደረግ እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል ።

**ሰንጠረዥ 1: የኢንዱስትሪ ዘርፍ የማስተሠርያ ተግባራትና አመታዊ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ዒላማዎች**

| የሙቀት አማቂ ጋዞች ማስተሰርያ ተግባራት ዒላማዎች | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ተግባራት | ዓመታዊ የሙቀት አማቂ ጋዞች ዒላማዎች (ሜት. ቶን የካርበን ዳይኦክሳይድ እኩሌታ/እ.አ.አ) | | | | | | | | | | | | አጠቃላይ ዒላማዎች |
| | | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | 2023 | 2024 | 2025 | 2026 | 2027 | 2028 | 2029 | 2030 | |
| 1 | የክሊንከር መተኪያ | 0.426 | 0.41 | 0.405 | 0.4 | 0.395 | 0.39 | 0.385 | 0.379 | 0.374 | 0.369 | 0.364 | 0.364 | 4.6 |
| 2 | ቆሻሻዎችን ለሀይል መልሶ በመጠቀም | 0 | 0 | 0.25 | 0.25 | 0.25 | 0.25 | 0.25 | 0.25 | 0.25 | 0.25 | 0.25 | 0.25 | 2.5 |
| 3 | ሀይልን በመቆጠብ | 0 | 0 | 0 | 0 | 1.06 | 1.06 | 1.06 | 1.06 | 1.06 | 0 | 0 | 0 | 5.3 |
| 4 | አማራጭ የነዳጅ ሀይሎች | 0 | 0 | 0.52 | 0.52 | 0.52 | 0.52 | 0.52 | 0.52 | 0.52 | 0.52 | 0.52 | 0.52 | 5.2 |
| 5 | አማራጭ የምርት ሂደቶች | 0 | 0 | 0 | 0.05 | 0 | 0 | 0.05 | 0 | 0.1 | 0 | 0.1 | 0.2 | 0.5 |
| 6 | የኢንዱስትሪዎችን የምርት ውጋጆች ማሻሻል | 0 | 0.095 | 0.152 | 0.19 | 0.285 | 0.38 | 0.475 | 0.57 | 0.665 | 0.95 | 1.33 | 1.9 | 1.9 |

*ምንጭ፤ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት ፍኖተ ካርታ (የአየር ንብረት ለውጥ እርምጃዎችን መከታተልና ማጠናከር)*

**ወደ ገፅ ፰**

**ከገፅ ፯ የቀጠለ...**

የኢንዱስትሪ ዘርፉ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይቀገር የአረንጓዴ ልማት ስልት ተግባራዊነትን እንዲደግፍ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተለያዩ ስትራቴጂካዊ እርምጃዎችንና ፕሮግራሞችን አዘጋጅቷል። ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፤

### 1. አረንጓዴ የአመራረት ስልት

ብሄራዊ አረንጓዴ የአመራረት ስትራተጂ የኢንዱስትሪ ልማት አካባቢያዊ፣ የአየር ንብረት፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖዎችን በሚዳስስ እና የውጭ ኢንቬስትመንትን ለመሳብ በሚያስችል መንገድን እ.አ.አ. በ2019 ተዘጋጅቶ ፀድቋል። ስትራቴጂው በአምራች ዘርፉ ላይ የሚስተዋሉ ዘላቂነትን የሚፈታተኑ ጉዳዮችን የሚዘረዝር ሲሆን እነዚህን ድክመቶች ለመቀነስ የሚረዱ ዒላማዎችና እርምጃዎችንም አካቶ ይዟል።

### 2. ሀይልን በውጤታማነት በአምራች ዘርፍ የመጠቀም ስልት

ለአምራች የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሀይል አጠቃቀም ውጤታማነት ስልት እ.አ.አ. በ2019 ተዘጋጅቶ ፀድቋል። ይህ ስልት በሀገሪቱ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት ላይ በአምራች ዘርፉ እንዲፈፀሙ የተቀመጡ ስትራቴጂካዊ ዒላማዎች ለማሳካት ይረዳል።

### 3. የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት የኮሙኒኬሽን ስትራተጂ ሰነድ

በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልትን ለማሳካት በኢንዱስትሪው ልማት ዘርፍ የአነስተኛ ልቀት መርህና ፋይዳዎቹን ለእድገት የሚያበረክተውን ጥቅሞች ለማስተማር ስልታዊ የኮሙኒኬሽን እቅድ ይፈልጋል። ለዚህ ሲባል የአረንጓዴ ማኑፋክቸሪንግ ኮሙኒኬሽን ዕቅድ ሰነድ ከአምራች ዘርፉና የአመራረት መርሆዎችና አሰራሮች ጋር ተጣጥሞ እ.አ.አ. በ2018 ተዘጋጅቶ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ የተከናወኑ የተለያዩ እርምጃዎችን ለማስተዋወቅ በስራ ላይ ውሏል።

## ከአረንጓዴ የአየር ንብረት ፈንድ (GCF) ሀብቶችን ለማግኘት የተደረጉ ጥረቶች

እ.ኤ.አ በ 2015 ለአረንጓዴ የአየር ንብረት ፈንድ (ጂ.ሲ.ኤፍ) ባለ ስድስት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ሰነድ ተዘጋጅቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር ቀርቧል ። የቀረበው ሀሳብ የኢንዱስትሪ ዘርፍን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን በመገደብ የሀገሪቱን በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ለመቀነስ የተጣሉ ግቦችን ለማሳካት የሚረዳ የሙከራ ኃይል ቆጣቢ ፕሮግራምን ለማሳደግ ተፈልጎ ነው። ከአረንጓዴ የአየር ንብረት ፈንድ የሚገኘው የፋይናንስ ሀብት ከፕሮጀክቱ ባለቤቶች እና ከፋይናንስ ተቋማት ተጨማሪ ሀብቶችን በፍትሃዊነት እና በብድር ላይ ለማዋል እንደ ዋስትና ሆኖ እንዲያገለግል ታስቦ የተቀረፀ ነበር። ሆኖም በአገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ልቀትን ለሚያወጡ ዘርፎች ቅድሚያ የተሰጠው በመሆኑ ሀሳቡ እንዲቀርብ አልተመረጠም ።

ይሁንና በቅርቡ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በጋራ ለአረንጓዴ የአየር ንብረት ፈንድ ፅንሰ-ሃሳብ አቅርበዋል። ፅንሰ-ሃሳቡ በሲሚንቶ ፋብሪካዎች ውስጥ የሚለቀቅ ሙቀትን መልሶ በሚጠቀም ስርዓት አማካኝነት የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን መቀነስ ላይ ያተኮረ ሲሆን በአጠቃላይ 21.95 ሚሊዮን ዶላር ለመሰብሰብ ያለመ ነው።

## የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ የተሻሻሉ የኃይል ውጤታማነት ልምዶች

ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን፣ ከዘርፍ ልማት ተቋማት፣ ከኢነርጂ ባለስልጣን፣ ከስኳር ኮርፖሬሽን፣ ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ እና ከክልል ኢነርጂ ቢሮዎች የተውጣጡ የኃይል አስተዳደር ቡድን እ.አ.አ. በ 2019 ስለ ሀይል አስተዳደርና የአጠባበቅ ስልቶች በቂ ግንዛቤን ለመጨበጥ የሚረዱ ተከታታይ ስልጠናዎች እና የፋብሪካ ጉብኝቶች ላይ ተሳትፈዋል።

**ወደ ገፅ ፱**

**ከገፅ ፰ የቀጠለ..**

ሰልጣኞቹ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሀይል አጠቃቀም ውጤታማነት ተግባራዊነት የሀይል አያያዝ ፕሮግራም ለማዘጋጀት የተገኘውን እውቀት ተጠቅመዋል። ተሳታፊዎችም ለአምራች ዘርፉ የመጀመሪያውን የብሔራዊ ኢነርጂ አያያዝ ስትራቴጂ ለማርቀቅ አግዘዋል።

የአንድ አካል የኃይል አጠቃቀምን መገምገም፣ የኃይል አጠቃቀምን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የድርጅታዊ እርምጃዎችን መመርመር እና የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመጥቀስ ለወደፊቱ የኃይል ጥበቃ ዒላማዎችን የሚመክር የኢነርጂ ማኔጅመንት ፕሮግራም ተቋቁሟል ።

እንደ ፋብሪካ ምርጫ መስፈርት የሀይል አስተዳደር ፕሮግራም ቡድኖች ከተለያዩ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች 13 ፋብሪካዎችን የመረጃ አሰባሰብ እና የሀይል አያያዝ ትግበራ መርጠዋል።

ከእነዚህ ፋብሪካዎች ውስጥ አስራ ሁለት (12) አሁን የታቀደውን የሀይል አያያዝ ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ በሂደት ላይ ናቸው።

**የኢንዱስትሪ ሂደት እና የምርት አጠቃቀም ዘርፍ የ ሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን የመለካት፣ ሪፖርት ማድረግና የማረጋገጥ ሂደት**

አሁን በስራ ላይ ያለውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን የመለካት፣ ሪፖርት የማድረግና የማረጋገጥ ሂደት ስርዓት ለማጠናከር እና ለማሻሻል የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከአውሮፓ ህብረት ጋር በመሆን የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት ኢንስቲትዩትን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን የተመለከቱ አስተማማኝ መረጃዎችን የማሰባሰብና የማስተዳደር አቅምን ለማሳደግ እና በለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት ትግበራ እርምጃ ላይ መሻሻል ለማምጣት ለሙቀት አማቂ ጋዞች የመረጃ አያያዝ ስርዐትን ለማዳበር እየሰራ ነው። በተጨማሪም የኢንዱስትሪ ሂደት እና የምርት አጠቃቀም ዘርፍ የቀጣይ 20 ዓመታት የሙቀት አማቂ ጋዞች ክምችት ኢንቨንተሪ በዝግጅት ላይ ይገኛል።

**ሰንጠረዥ 2: የሀይል አስተዳደርና ትግበራ ፕሮግራም**

| ተ.ቁ. | ዘርፍ | ፋብሪካ | የሚገኝበት ቦታ | የትግበራ ደረጃ | የታቀደ አጠቃላይ የልቀት ቅነሳ ዕቅድ (በ ኪግ ካርበን ዳይኦክሳይድ ዕኩላታ/በዓመት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቆዳ/ሌጦ | ባቱ የቆዳ ፋብሪካ | አዲስ አበባ | በትግበራ ላይ ያለ | 1,221,646.00 |
| | | ኮልባ ታነሪ ፒ.ኤል.ሲ. | ሞጆ | በትግበራ ላይ ያለ | 534,990.47 |
| 2 | ስጋና ወተት | አል ኑጁም ኤክስፖርት ቄራ | ዱከም | በትግበራ ላይ ያለ | 501,349.13 |
| | | አደአ ወተት | ቢሾፍቱ | በትግበራ ላይ ያለ | 64,392.64 |
| 3 | ብረት | ስቲሊ አር.ኤም.አይ. | ቢሾፍቱ | በትግበራ ላይ ያለ | 13,833,961.65 |
| | | የሱ ፒ.ኤል.ሲ. | ገላን | በትግበራ ላይ ያለ | 3,179,636.359 |
| 4 | ኬሚካል | አዲስ አበባ መስታወት ፋብሪካ | አዲስ አበባ | በትግበራ ላይ ያለ | 3,191,773.935 |
| | | ማናዬ አሻጊዎች | አለም ገና | በትግበራ ላይ ያለ | 1,342,116.45 |
| 5 | ምግብና ለስላሳ መጠጦች | ሮራንክ ሼር ኩባንያ | ጫጫ | በዝግጅት ላይ ያለ | - |
| | | ሻንግ ፋርማሲቲካል | ዱከም | በትግበራ ላይ ያለ | 264.12 |
| 6 | የጥጥ ምርት | ካኖሪያ አፍሪካ የጥጥ ፋብሪካ | ቢሾፍቱ | በትግበራ ላይ ያለ | 983,638.63 |
| | | ኤልሳ አዲስ ኢንዱስትሪያል ፒ.ኤል.ሲ | አዳማ | በትግበራ ላይ ያለ | 1,048,692.05 |
| 7 | ስኳር | ወንጂ ስኳር ፒ.ኤል.ሲ. | ወንጂ | በትግበራ ላይ ያለ | 617.28 |

# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

የኢፌዴሪ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን
ሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
ፖ.ሳ.ቁ : 12760, አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ ቁጥር: +251 11-170-4038/4150
ኢሜል: efcccethiopia@gmail.com
ድረ ገፅ: https://www.efccc.gov.et

## ሀላፊነት ስለመውሰድ

በዚህ ህትመት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች የግድ የኢትዮጵያን መንግስት ኦፊሴላዊ አመለካከቶችና ፖሊሲዎች የሚወክሉ አይሆኑም። በተጨማሪም ሌሎች ሀገራትንና ተቋማትን የሚመለከቱ አንዳንድ ይዘቶች ቢኖሩ እነዚህ ሀገራቱን የተመለከቱ ጉዳዮች የሀገራቱን የህጋዊ መብት የሀገር ድንበር፣ ወይም ከተማና የስልጣን ሁኔታዎች የኢትዮጵያ መንግስትንም ሆነ ህትመቱን በገንዘብና በቴክኒክ የደገፉ ተቋማት ፖሊሲዎች ወይም አቋሞችን የሚወክሉ አይደሉም።

## ስራውን የደገፉ አካላት

IN CONTRIBUTION TO THE NDC PARTNERSHIP

Supported by:

Funded by

This work was carried out with the aid of a grant from the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands and the International Development Research Centre (IDRC), Canada, as part of the Climate and Development Knowledge Network (CDKN) Programme. The views expressed herein do not necessarily represent those of the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands, or of the International Development Research Centre (IDRC) or its Board of Governors, or of the entities managing CDKN.